# Bibliothèques Municipales
*une fenêtre sur le monde*

# ወደ ጄኔቫ ማዘጋጃ ቤት ቤተ-መጻሕፍት መረብ እንኳን ደህና መጡ!

ለእርስዎ ወይም ለልጆችዎ መጽሐፍ፣ ሲዲ ወይም ዲቪዲ እየፈለጉ ነው? በይነመረብን ማሰስ ወይም ኢሜልዎን ምቹ እና ጋባዥ በሆነ ቦታ ለመመልከት ይፈልጋሉ? ቡና እየጠጡ ተወዳጅ ጋዜጣዎን ማንበብ ይፈልጋሉ? የማዘጋጃ ቤቱ ቤተ መጻሕፍቶች አሉልዎ፤ እነሱም ነፃ ናቸው። ከ 500,000 በላይ መጽሐፎችን እና ሰነዶችን፣ 80,000 ሲዲዎችን እና 50,000 ዲቪዲዎችን ያቀርባሉ። እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ራሽያኛ፣ አረብኛ፣ ስፓንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ፖርቱጋልኛ እና አልባኒያኛን ጨምሮ በርካታ መጽሐፎች፣ መጽሔቶች፣ ዲቪዲዎች፣ ጋዜጣዎች ወ.ዘ.ተ. በብዙ ቋንቋዎች ይገኛሉ። የቤተ መጻሕፍት ባለሙያዎቹ እርስዎን ተቀብለው በምርምርዎ ውስጥ መምራት ያስደስታቸዋል። በማዘጋጃ ቤቱ ቤተ መጻሕፍቶች በመገኘትዎ በጣም ደስተኞች ነን። አይዘግዩ፣ ይምጡና ይጎብኙን!

**Sami Kanaan /ሳሚ ከንዓን/**
የከተማው የባህል እና ስፖርት
መምሪያ ተጠሪ አማካሪ

## የ ማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት የአገልግሎት መረብ

የ ማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት መረብ 7 ቤተ-መጻሕፍትን እና የቤተ-መጻሕፍት የአውቶቡስ አገልግሎትን የያዘ ነው። ይህም ለአዋቂዎች እና ወጣቶች በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ላይ እና በሁሉም የመገናኛ ዘዴዎች ለመረጃ፣ ትምህርት፣ ባህል እና ለመዝናኛ አላማዎች ሰነዶችን ለመመርመር እና ለመዋስ የሚያስችል ቦታን ያቀርባል። የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች ከሞላ ጎደል በሁሉም የከተማው ዲስትሪክቶች ውስጥ ይገኛሉ።



### እንዴት ነው የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት[1] መረብን የሚያገኙት?

የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ስብስቦች እና አገልግሎቶች ክፍት እና በነጻ የሚገኙ ናቸው። ሁሉንም የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ሰነዶች ከክፍያ ነጻ መዋስም ይቻላል፣ ነገር ግን ይህ ምዝገባ እና መታወቂያ ማሳየት ይጠይቃል። ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ለምዝገባ ከወላጆቻቸው ወይም ከሕጋዊ ተወካይ ፈቃድ (ፊርማ) ያስፈልጋቸዋል። ቀጥሎም የተዋሸ ካርድ በቤትዎ አድራሻ ይላካል። ምዝገባው ለጄኔቫ ክልል ነዋሪዎች ወይም ማዘጋጃ ቤታቸው ከጄኔቫ[2] ከተማ ጋር የትብብር ስምምነት ለተፈራረሙ የተቀመጠ ነው። ሙሉ ዝርዝሮች (አድራሻ፣ የመክፈቻ ሰዓቶች፣ ስልክ) በ "የመክፈቻ ሰዓቶች" ሰነድ እና በማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ድርጣቢያ፡ **www.bm-geneve.ch** ላይ ይቀርባል::

## የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች የሚያቀርቧቸው ባለ ብዙ ቋንቋ ስብስቦች ምንድን ናቸው?

**ለአዋቂዎች፡**
- **ልብ ወለዶች፡** እንግሊዝኛ፣ ጀርመን፣ ጣሊያንኛ፣ ስፓኒሽ፣ ፖርቱጋልኛ
- **የህትመት ሚዲያ፡** እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ራሽያኛ[3]፣ አረብኛ[3]፣ ስፓንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ፖርቱጋልኛ
- **ዲጂታል ሚዲያ፡** ከ 100 በላይ በሆኑ የውጭ ቋንቋዎች ከ 7,000 በላይ ርዕሶች
- **የኦዲዮ መጻሕፍት[3]፡** በእንግሊዝኛ እና በጀርመንኛ
- **ኢ-መጻሕፍት:** በእንግሊዝኛ

**ለወጣቶች፡**
- **መጻሕፍት፡** እንግሊዝኛ፣ ጀርመንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ስፓንኛ፣ ፖርቱጋልኛ፣ አረብኛ፣ አልባኒያኛ፣ ራሽያኛ

በተጨማሪም የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች ለውጭ ቋንቋዎች እና ፈረንሳይኛ የትምህርት መርሃ ግብሮችን ያቀርባል።

## የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ስብስቦች ምንን ያካትታሉ?

ለእያንዳንዱ የዕድሜ ቡድን፣ ቤተ-መጻሕፍቶቹ የሚከተሉትን ያቀርባሉ፡
- ዶክመንተሪዎች
- ልብ ወለዶች
- አስቂኞች
- አልበሞች
- መጽሔቶች እና ዕለታዊ ጋዜጦች
- በትላልቅ ህትመቶች የታተሙ ልብ ወለዶች
- የሙዚቃ ስብስቦች
- የመልቲሚዲያ ስብስቦች (ልብወለድ ፊልሞች፣ ዘጋቢ ፊልሞች፣ የኦዲዮ መጻሕፍት፣ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞች)
- ዲጂታል መርጃዎች (ኢ-መጻሕፍት፣ መጽሔቶች እና ዕለታዊ ጋዜጦች፣ የግል-ጥናት፣ የተለቀቀ ሙዚቃ)

## የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ?

የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች ለስራ፣ ለንባብ፣ እና ለማዳመጥ የሚሆኑ ቦታዎች እና የ WIFI ግንኙነቶች አሏቸው።
በተጨማሪም ለ 45 ደቂቃ ክፍለ ጊዜ በቦታው ላይ ወይም በስልክ አስቀድመው ሊያዙ የሚችሉ በይነ መረብ ማሰስ የሚችሉባቸው ኮምፒዩተሮችን ማግኘት ይችላሉ። የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶችን የመስመር ላይ ካታሎግ ለመፈለግ የሚያገለግሉ ኮምፒዩተሮችም ይገኛሉ። በርካታ ከክፍያ ነፃ የሆኑ የሥነ ጥበብ ተነሳሽነቶች እና የስልጠና ወርክሾፖች ለሁሉም ዕድሜ እና ምርጫዎች ዓመቱን ሙሉ ይቀርባሉ፡ ተጨማሪ ለማወቅ የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ፕሮግራምን ወይም ድር ጣቢያ ይመልከቱ! የሰነዶች ርዕሰ ጉዳይ ምርጫዎችን እንዲያገኙ ለማስቻል ዋቢ ጽሑፎች፣ ዲስክግራፊዎች እና ጦማሮች (blog-bmgeneve.ch) ይገኛሉ። የመስመር ላይ ካታሎጉ https://collectionsbmu.ville-ge.ch ሁሉንም የማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት ክምችቶች እንዲሁም ከርቀት ውሰትዎችዎን ለማስተዳደር የ "My Space" አማራጭን ለማስተዳደር ይፈቅድልዎታል። የተዋሸ ካርድዎ እንደደረስዎ የመዳረሻ ኮድ ይሰጥዎታል።

በማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍት መረብ ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች ሁሉ ለጥያቄዎችዎ መልስ ለመስጠት እና ምርምርዎን ለማገዝ ይገኛሉ።

[1] የምዝገባ እና ውሰት ውል እና ሁኔታዎች በማዘጋጃ ቤተ-መጻሕፍቶች የአቃቀም ፖሊሲ ውስጥ በዝርዝር ተቀምጠዋል።
[2] Nyon, Ambilly, Annemasse, Collines du Léman, Divonne-les-Bains, Evian, Gex, Lucinges, Saint-Genis-Pouilly, Thonon-les-Bains, Saint-Cergues (FR) Saint-Julien-en-Genevois, Veigy-Foncenex, Ville-la-Grand, Bellegarde
[3] የሚገኘው በ Bibliothèque de la Cité ብቻ ነው።